የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፺
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.90
ADDIS ABABA , 8th September , 2017

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፪/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን እና ሀይጂን ብሄራዊ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……………………………………………………ገፅ ፱ሺ፱፻፰

CONTENT

Proclamation No.1042/2017

African Development Fund Additional Loan Agreement for Financing Water, Sanitation and Hygiene National Program Ratification Proclamation…………………………page 9908

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፪/፪ሺ፱

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን ተጨማሪ የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን እና ሀይጂን ብሄራዊ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፪ ሚሊዮን ፪፻፺ ሺህ ዩ.ኤ (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ዩ.ኤ) የሚያስገኘው ተጨማሪ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው

## PROCLAMATION No. 1042/2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE ADDITIONAL LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

**WHERE AS,** the Additional Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Government of the Federal Democratic Republic Of Ethiopia a Loan amount of 2,290,000 Units of Account (Two Million Two Hundred and Ninety Thousand Units of Account) for financing Water, Sanitation and Hygiene National Program (OWNP), was signed in Addis Ababa on the 24th day of May 2017;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 5th day of July , 2017;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

www.chilot.me

ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን እና ሀይጂን ብሄራዊ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፪/፪ሺ፱ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2100150037344 በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፪ ሚሊዮን ፪፻፺ ሺ ዩ.ኤ (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ዩ.ኤ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጳጉሜ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

ሙላቱ ተሾመ ዶ/ር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of the Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "African Development Fund Additional Loan Agreement for financing Water, Sanitation and Hygiene National Program Ratification Proclamation No.1042/2017".

## 2. Ratification of the Agreement

The Additional Loan Agreement Number 2100150037344 signed in Addis Ababa on the 24th day of May 2017 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 2,290,000 Units of Account (Two Million Two Hundred and Ninety Thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Additional Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of September,2017**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

www.chilot.me